በኢትዮጵያ

ብዙኃን መገናኛዎችና ባለሙያዎች ዘንድ
የካቲት ወር እንዴት አለፈ?

ወርኃዊ አጭር ዳሰሳ

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር

EMMPA
የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር
Ethiopian Mass Media Professioals Association

መጋቢት 1 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ

ወሩ እንዴት አለፈ?

የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር ከዚህ ጀምሮ የኢትዮጵያን የመገናኛ ብዙኃን ትግበራና የጋዜጠኞች እንቅስቃሴ በተመለከተ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ወርሃዊ ጭምቅ ዳሰሳ የሚያቀርብ ይሆናል።

ባሳለፍነው የካቲት ወር የነበሩ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ነበሩ።

ሀ) መገናኛ ብዙኃንና የ2013 ዓም ምርጫ

የፓርቲዎች ምርጫ ዘመቻ ባሳለፍነው የካቲት ወር የመጀመሪያ ሳምንት በይፋ ተጀምሯል። ይህንን የየፓርቲዎቹን የምርጫ ዘመቻ ማስጀመሪያ ስነ ስርዓት ሚዲያዎች ለገዥው ፓርቲም ይሁን ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የዘገባ ሽፋን ሲሰጡ ተስተውሏል።

የግልም ይሁን የ " መንግስት " ብዙኃን መገናኛዎቹ የመጀመሪያው ሰሞን የፓርቲዎችን የምርጫ ዘመቻ ማስጀመሪያ ስነ ስርዓቶች ሽፋን መስጠታቸው መልካም ጅምር ሆኖ አልፏል።

ይሁንና የዘገባ ሽፋናቸው ምጣኔ በግርድፉ ሲታይ ውግንና የተስተዋለበት ነበር ማለት ይቻላል። በተለምዶ የ "መንግስት " የሚባሉትና ለገዥው ፓርቲ ቅርበት ያላቸው ብዙኃን መገናኛዎች ለገዥው ፓርቲ ሰፋ ያለ ሽፋን ሲሰጡ በተመሳሳይ በተለምዶ የግል የሚባሉት ደግሞ ለ " ተፎካካሪዎች" ሰፋ ያለ ሽፋን ሰጥተዋል። ይህ በሁሉም ዘርፎች ማለትም በ መደበኛ ብዙኃን መገናኛዎች " Mainstream Media " እና በ አዲሱ ትውልድ ብዙኃን መገናኛዎች " Social/New Media " የተስተዋለ ነው።

ይህ በብዙኃን መገናኛዎቹ የተስተዋለው የ " ፓርቲ ውግንና ዝንባሌ " በሚቀጥሉት ጊዜያት በሚኖረው ነፃና ፍትሃዊ የምርጫ አዘጋገብና የምርጫ መረጃ ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ስጋት አለን።

በመሆኑም የብዙኃን መገናኛዎች መማክርት /Media Council/ ፣ የጋዜጠኞች ማህበራት፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣንና ሌሎች ባለድርሻዎች በምርጫ ዘገባና ሽፋን ዙሪያ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል። አሳታፊ በሆነ መልኩ ጊዜያዊ ኮሚቴ ቢቋቋም መልካም መሆኑን ማህበራችን ይጠቁማል።

ለ) ዓለም አቀፍ ዘጋቢዎችና ትግራይ ክልል

ባሳለፍነው ወር ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ብዙኃን መገናኛ ዘጋቢዎች በትግራይ ክልል ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ በተመለከተ እንዲዘግቡ የኢትዮጵያ መንግስት ፈቃድ ሰጥቷል። ሰባት ለዓለም አቀፍ ብዙኃን መገናኛዎች የሚዘግቡ ጋዜጠኞችም ወደ ትግራይ በመጓዝ ዘገባዎችን ተደራሽ አድርገዋል።

ምንም እንኳን የዘገየ ቢሆንም ጋዜጠኞች እንዲዘግቡ መደረጉን ማህበራችን በመልካም ጎን ተመልክቶታል።

ይሁንና በተወሰኑ ጋዜጠኞች በተለይም በቢቢሲ ትግርኛና ኤ ኤፍ ፒ ጋዜጠኞችና የጋዜጠኞች ረዳቶች ላይ የተፈፀመው እስርና የደረሰው እንግልት ፍፁም ተቀባይነት የሌለውና የኢትዮጵያን የፕሬስ ነፃነት እንደገና ቀድሞ ወደነበረበት አስከፊ ገፅታ የመመለስ ሂደት በመሆኑ ማህበራችን አጥብቆ የሚያወግዘው ተግባር ነው።

ጋዜጠኝነት በነፃነትና ሙያዊ ስነ ምግባርን በጠበቀ መልኩ የሚተገበርባት ኢትዮጵያ እንድትኖረን ማህበራችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሁሉ በትብብር ለመስራት ቁርጠኛ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እያሳወቅን በተቃራኒው በጋዜጠኞችና በብዙኃን መገናኛ ተቋማት ዘንድ ሙያዊ ነፃነትን፣ ለህዝብና እውነት ወገንተኝነትን የሚያሰናክሉ ሁኔታዎችን አጥብቀን የምንታገል ይሆናል።

በተጨማሪም ለህዝብ ከስፍራው ሚዛናዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲደርስ ብዙኃን መገናኛዎች ያላቸውን ሚና እንዲወጡ ለዓለም አቀፍ ብዙኃን መገናኛዎች የተፈቀደው ዕድል ለአገር ውስጥ የግል ብዙኃን መገናኛዎችም መፈቀድ እንዳለበት ማህበራችን ያምናል።

ሐ) አዳዲሶቹ የሚዲያ ህጎች እና ከብሮድካስት ወደ የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ማደግ

በቅርቡ በኢትዮጵያ ጋዜጠኝነትና ብዙኃን መገናኛ አውደ ታሪክ በበጎ ሊነሱ ከሚገባቸው ጉዳዮች መኃል አገራዊ የ" ሚዲያ ፖሊሲ " መዘጋጀት አንዱ ነበር። የብዙኃን መገናኛ አዋጅም በቅርቡ መፅደቁ ይታወሳል።

ባሳለፍነው ወር ደግሞ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ወደ ኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ቅርፁን የሚቀይር አዋጅ ፀድቋል።

ቀድሞ የነበረውን ክፍተት ግምት ውስጥ ያስገባና ሁሉንም አይነት ብዙኃን መገናኛዎች ማዕከል ያደረገ ተቋም እንዲሆን መደረጉ መልካም ነገር መሆኑን ማህበራችን ያምናል።

በፖሊሲው መውጣትም ሆነ በባለስልጣኑ ቅርፅ መለወጥ የኢትዮጵያ ብዙኃን መገናኛ ተቋማትና ባለሙያዎች የሚያገኙት መልካም ዕድል መኖሩን በመገንዘብ ማህበራችን በሂደቱ ለተሳተፉ የሚዲያ ምሁራን፣ የህግ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻዎች ሁሉ ምስጋና ያቀርባል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በፖሊሲውና በአዋጁ የተገኙና የሚገኙ መልካም ትሩፋቶችን በትክክል እንዲተገበሩና የኢትዮጵያ ጋዜጠኝነትና ብዙኃን መገናኛ ተቋማት አውድ እንዲያድግ ሁሉም ባለድርሻዎች መረባረብ ይኖርባቸዋል። ይህ ባለመሆኑና ምናልባትም ከአዋጁ፣ ፖሊሲውና ተያያዥ ህጎች ባፈነገጠ መልኩ እንዲተገበር ጫናዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ከቀደመውና ካሳለፍነው የከፋ የፕሬስ ነፃነት ማጣት ብሎም የባለሙያዎች እስርና እንግልት እንዲበራከት መፍግኤ ይሆናል።

ማህበራችን ፖሊሲው፣ አዋጁና ተያያዥ የትግበራ ህጎች ሁሉ (ድክመታቸቸው ሳይዘነጋ) በወረቀት ላይ በተፃፉበት ልክ እንዲተገበሩ ይሰራል፣ የጋዜጠኝነት ስነ ምግባርና በሙያዊ ዕውቀት የላቀ ትግበራ እንዲስፋፋ እንዲሁም የሙያ ነፃነት እንዲጎለብት የሚጠበቅበትን ይወጣል። ከአዲሱ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣንም የተሻለ አሰራር ይጠብቃል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለብዙኃን መገናኛዎችና ባለሙያዎች ነፃነትና የስራ ትግበራ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችና እንግልቶች እንዲቀረፉም በንቃት የሚሰራ ይሆናል።

በዚህ አጋጣሚ በቅርቡ የስልጣን መልቀቂያ ያስገቡት የባለ ስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ዶር ጌታቸው ድንቁ በቀጣይ ህይወታቸው መልካሙን ሁሉ እንዲያጋጥማቸው እየተመኘን ለጋዜጠኝነትና ስነ ተግባቦት ሙያዎች ዕድገት ምሁራዊ አበርክቷቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ አደራ እንላለን።

መ) የጋዜጠኛ ሰለሞን ገብረ መድኅን ህልፈት

የደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ባልደረባ የነበረው ጋዜጠኛ ሰለሞን ገ/መድህን በአደረበት ህመም በህክምና ሲረዳ ቆይቶ በ48 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ባሳለፍነው የካቲት ወር ነበር።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የ2ኛ ዲግሪ በጆርናሊዝም እና በማስ ኮምዩኒኬሽን የተመረቀውና በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችን ህዝቦች ክልል በማስታወቂያ ቢሮ የጋዜጣ ዝግጅት ረዳት አዘጋጅ ሆኖ ከተቀጠረበት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በኋላም በደቡብ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት አሁን ደግሞ በደቡብ

ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በአዘጋጅነት፣ በከፍተኛ አዘጋጅነት፣ በአርታኢነት፣ በምክትል አዘጋጅነትና በዋና አዘጋጅነት ከፍተኛ ሙያዊ አስተዋፅኦ ያበረከተ ነበር።

በድጋሚ ለቤተሰቦቹና ወዳጆቹ ማህበራችን መፅናናትን ይመኛል።

//

መጋቢት 1 ቀን 2013 ዓም
አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር
etjournalists@gmail.com